# በፖሊስ ጣቢያ ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ የእርስዎ መብቶች

የልጆች እና ታዳጊዎች መመሪያ

**ይህ በራሪ ወረቀት በፖሊስ ጣቢያ ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ ስላለዎት መብቶች አስፈላጊ መረጃ ይሰጥዎታል።** መብቶች ሁላችንም ያሉን በህግ የተጠበቁ ነጻነቶች እና ድጋፎች ናቸው። ከ 18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች የተወሰኑ ከአዋቂዎች የተለዩ መብቶች አሏቸው፤ ስለዚህ ይህ በራሪ ወረቀት ያልዎትን መብቶች ያብራራል።

**መብቶችዎን ማወቅ እና መረዳት በትክክል መስተናገድዎን እንዲያውቁ ያግዝዎታል።** ፖሊሱ ምንም እንኳን ጉዳት የሚያስከትል ነገር መስራትዎን የሚጠቁም ማስረጃ ቢኖረው እንኳ፣ በፖሊስ ጣቢያ ውስጥ እርስዎን ከጉዳት የመጠበቅ እና ደህንነትዎን የመከታተል ግዴታ አለበት። .

**በተቻለ ፍጥነት ይህንን በራሪ ወረቀት ያንብቡት።** ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ ውሳኔዎችን ለማድረግ ያግዝዎታል። ይህንን በራሪ ወረቀት የሰጠዎት ሰው በማንበብ እና እንዲረዱት በማድረግ ያግዝዎታል። በሌላ ቋንቋ ወይም ለማንበብ ቀላል የሆነ የዚህን በራሪ ወረቀት ሌላ ስሪት ይፈልጉ እንደሆነም ይጠይቁዎታል።.

Children and Young People's Centre for Justice

STARR

Safer Scotland
Scottish Government

1. **ፖሊሱ ለምን በፖሊስ ጣቢያ እንደሚያቆይዎ የማወቅ መብት አለዎት።**

2. **ፖሊሱ ለምን ወደ ፖሊስ ጣቢያ እንዳመጣዎ የማወቅ መብት አለዎት።**





3. እነዚህን ካወቁ ለፖሊስ ስምዎን፣ አድራሻዎን፣ የትውልድ ቀን እና ዜግነትዎን መስጠት አለብዎ። መመለስ ያለብዎት ጥያቄዎች እነዚህን ብቻ ናቸው። **ማንኛውንም ሌሎች ጥያቄዎች ያለመመለስ መብት አለዎት።**

4. **ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ እንደሆኑ ለአንድ ሰው የመናገር መብት አለዎት።** ፖሊሱ እዚያ መሆንዎን ለአንድ ሰው መንገር ይፈልጉ እንደሆነ ይጠይቅዎታል። ይህ በቤተሰብዎ ውስጥ ላለ ሰው፣ ለአጋርዎ፣ ለተንከባካቢዎ፣ ለጓደኛዎ ወይም ለሌላ ለማንኛውም ለሚያውቁት ሰው ሊሆን ይችላል። እንዲያነጋግሯቸው ላይፈቀድልዎት ይችላል። ከ16 ዓመት በታች ከሆኑ ወይም በአስገዳጅ ቁጥጥር ትዕዛዝ ላይ ካሉ በፖሊስ ጣቢያ ውስጥ ከአንድ ሰው ጋር የመሆን መብት አለዎት። በፖሊስ ጣቢያ ውስጥ ወላጅዎ ወይም በአሳዳጊዎ የመጎብኘት መብት አለዎት። .

5. **በፖሊስ ጣቢያ ውስጥ መሆንዎን ለጠበቃ የመናገር መብት አለዎት።** ፖሊሱ ፖሊስ ጣብያ ውስጥ መሆንዎን ለጠበቃዎ መንገር ይፈልጉ እንደሆን ይጠይቅዎታል። ይህ የራስዎ ጠበቃ ወይም ዝግጁ ጠበቃ ሌላ ጠበቃ ይዘጋጅልዎታል። ነጻ ነው። .



6. **በማንኛውም ጊዜ ከጠበቃው ጋር በግል የመነጋገር መብት አለዎት።** ነጻ ነው።

7. **ፖሊሱ ቃለ መጠይቅ እያደረገልዎት ከሆነ ጠበቃ እንዲገኝ የማድረግ መብት አለዎት።** ነጻ ነው።

8. **ከ16 ዓመት በታች ከሆኑ፣ አንድ ሰውን አደጋ ላይ ካልጣለ በስተቀር ፖሊሱ ቃለ መጠይቅ በሚያደርግልዎት ጊዜ ጠበቃ መገኘት አለበት።** እድሜዎ 16 ወይም 17 ከሆነ እና በአስገዳጅ የቁጥጥር ትዕዛዝ ላይ ከሆኑ፣ የተለዩ ሁኔታዎች ከሌሉ በስተቀር ፖሊሱ ቃለ መጠይቅ በሚያደርግልዎት ጊዜ ጠበቃ መቅረብ አለበት።

9. **ከታመሙ ወይም ከተጎዱ የህክምና እርዳታ የማግኘት መብት አለዎት። ይህ የአዕምሮ ጤናዎንም ያጠቃልላል።** ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ በሚገባ እንክብካቤ እንዳገኙ ለማረጋገጥ እንዲረዳ ስለ ጤናዎ እና ደህንነትዎ ጥያቄዎችን ይጠይቁዎታል። ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ የሚጎዳዎ የህክምና ሁኔታ ካለዎት ለፖሊስ መናገር አስፈላጊ ነው። ፖሊሱ እንዲያክምዎ ሃኪም ወይም ነርስ ሊጠይቁ ይችላሉ። ይህ ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ በሚገባ እንክብካቤ እንዳገኙ ለማረጋገጥ እንዲረዳ ነው። ፖሊሱ ሃኪም፣ ነርስ፣ ወይም ሌላ የጤና ባለሙያ ማነጋገር ይፈልጉ እንደሆነ ሊጠይቁዎት ይገባል።

10. **ማግብ እና መጠጥ የማግኘት መብት አለዎት።** ውሃ ይቀርብልዎታል። በፖሊስ ጣቢያ ውስጥ ከአራት ሰአታት በላይ ከቆዩ ምግብ ይሰጥዎታል። ፖሊስ ማንኛውም የተለየ የአመጋገብ ፍላጎት እንዳለዎት መጠየቅ አለበት።

# ተጨማሪ መመሪያ...

## ተጨማሪ እርዳታ ከፈለጉ

ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ ምን እየተከሰተ እንደሆነ ለመረዳት እገዛ ሊያስፈልግዎት ይችላል። እድሜዎ 16 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ፣ ይህ እርዳታ ተገቢ አዋቂ ተብሎ ከሚጠራው የሰለጠነ ድጋፍ ሰጪ ሰው ሊሆን ይችላል። የመማር እክል ወይም የአዕምሮ ጤና ችግር ካለብዎ ይህ ሊያስፈልግ ይችላል። ፖሊሶች ተገቢ የሆነ የአዋቂ ሰው እርዳታ እንደሚያስፈልግዎት ካሰበ፣ ባይጠይቁም እንኳ፣ ያመጡልዎታል።

## እርስዎን ለመርዳት አስተርጓሚ ማምጣት

ፖሊስ ጣቢያ የሚነገረውን መረዳት መቻልዎ አስፈላጊ ነው። እንግሊዝኛ የማይናገሩ ወይም የማይረዱ ከሆነ፣ ፖሊሶች የእርስዎን ቋንቋ የሚናገር ሰው እንዲረዳዎ ያመጡልዎታል። ይህ ሰው አስተርጓሚ ይባላል። ነጻ ነው።

## በግንኙነት ላይ እገዛን ማግኘት

ብዙ ሰዎች በፖሊስ ጣቢያው ውስጥ ምን እየሆነ እንዳለ ለመረዳት ይከብዳቸዋል። ፖሊስ እርዳታ ከፈለጉ ወይም ስለ ማንኛውም ነገር እርግጠኛ ካልሆኑ ሊጠይቅዎት ይገባል። ከፈለጉት በማንበብ እርዳታ ሊሰጡዎት ይገባል። መስማት የተሳንዎት ከሆኑ ወይም በግልጽ የመግባባት ችግር ካጋጠመዎት ፖሊስ የሚረዳዎት ሰው ያገኛልዎታል። ይህ የBSL አስተርጓሚ ወይም ሌላ ተገቢ ባለሙያ ሊሆን ይችላል። ነጻ ነው።

## ብሪቲሽ ካልሆኑ

የብሪትሽ ዜጋ ካልሆኑ፣ የት እንዳሉ እና ለምን በፖሊስ ጣቢያ ውስጥ እንዳሉ ለመንገር ፖሊስ ከፍተኛ ኮሚሽንዎን፣ ኤምባሲን ወይም ቆንስላ ጽህፈት ቤቱን እንድያነጋግሩ ሊጋብዝዎ ይገባል። ከዚያ በኋላ አንድ ሰው በግል ሊጎበኝዎት እና ጠበቃ እንዲያይዎ ሊያዘጋጅልዎት ይችላል።

## በትዕዛዝ ከተከሰሱ ወይም ወደ ፖሊስ ጣቢያ ከመጡ ምን ይከሰታል?

በወንጀል ከተከሰሱ፣ እንዲወጡ ሊፈቅድልዎት ወይም በፖሊስ ጣቢያ ሊቆዩ እና በሚቀጥለው ቀን ወደ ፍርድ ቤት ሊወሰዱ ይችላሉ። በማዘዣ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ከመጡ፣ በሚቀጥለው ቀን ተይዘው ፍርድ ቤት ሊቀርቡ ይችላሉ። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ ወደ ቤት እንዲሄዱ ሊፈቀድልዎት ይችላል።

## ለምን ያህል ጊዜ በቁጥጥር ላይ ሊቆዩ ይችላሉ?

ፖሊስ በወንጀል ክስ ሳይከስዎት እስከ 12 ሰዐታት ድረስ በቁጥጥር ስር ሊያቆይዎት ይችላል። ፖሊስ ይህንን ቢበዛ ለ24 ሰዓታት ሊያራዘም ይችላል ነገር ግን ከፍተኛ የፖሊስ መኮንኑ በዚህ ከተስማማ ብቻ ነው። ስለዚህ ውሳኔ አስተያየትዎን የመስጠት መብት አልዎት ወይም ጠበቃዎ ለእርስዎ ፖሊስን እንዲያነጋግር መምረጥ ይችላሉ። .

## የወረቀት ስራዎችን ማየት

ጉዳይዎ ወደ ፍርድ ቤት የሚሄድ ከሆነ፣ በጉዳዩ ላይ ያለውን የማስረጃ ማስታወሻ ለእርስዎ ወይም ለጠበቃዎ ይሰጥዎታል። ይህ እርስዎ ወይም ጠበቃዎ መከላከያዎን እንዲያዘጋጁ ያስችልዎታል። ይህ መረጃ እንዲተረጎም፣ ወይም እንግሊዝኛ ካልተረዱ ቢያንስ አስፈላጊ የሆኑትን የወረቀት ስራዎች ትርጉም የማግኘት መብት አለዎት።

CYCJ Children and Young People's Centre for Justice

STARR

Safer Scotland Scottish Government

# ተጨማሪ መመሪያ...

**ጠበቃ ስለማግኘት መብት መረጃ**

- ፖሊስ ጠበቃ ማነጋገር ይፈልጉ እንደሆነ ይጠይቅዎታል። ፖሊስ በተቻለ ፍጥነት ጠበቃ ያነጋግርዎታል።
- በማንኛውም ጊዜ ከአንድ ጠበቃ ጋር የግል ውይይት ለማድረግ ይፈቅድልዎታል። ይህ በስልክ ሊሆን ይችላል፣ ወይም ፖሊስ ጣቢያ መጥተው ሊያዩዎት ይችላሉ።
- ጠበቃ ማነጋገር የተለመደ ነው፣ እና ማንኛውንም ስህተት የሰሩ አያስመስልዎትም።
- የጠበቃ ስራ መብቶችዎን መጠበቅ እና ስለ ህጉ ምክር መስጠት ነው።
- እርስዎ የሚያውቁትን ጠበቃ ወይም ፖሊሱ እንዲያነጋግሩት ካዘጋጀልዎት ጠበቃ ጋር ለመነጋገር መምረጥ ይችላሉ – ይህ ጠበቃ ዝግጁ ጠበቃ ይባላል። ዝግጁ የሆነው ጠበቃ ራሱን የቻለ ሲሆን ለፖሊስ የሚሰራ አይደለም።
- ፖሊስ ቃለ መጠይቅ ካደረገልዎት፣ ይህ በሚሆንበት ጊዜ በክፍሉ ውስጥ ጠበቃ እንዲኖር ይፈልጉ እንደሆን ይጠይቅዎታል።
- ጠበቃ ከእርስዎ ጋር ክፍል ውስጥ እንዲኖር ከጠየቁ ፖሊስ ያለ ጠበቃ ቃለ መጠይቅ እንዲያደርልዎት አይፈቀድለትም።
- ከጠበቃ ጋር ስለመነጋገር ሃሳብዎን መቀየር እና በማንኛውም ጊዜ ጠበቃ መጠየቅ ይችላሉ። በተቻለ ፍጥነት ለፖሊስ ይንገሩ እና ጠበቃ ያነጋግሩልዎታል።
- ጠበቃው እንደሚመጡ ተናግረው ወደ ፖሊስ ጣቢያ ካልመጡ፣ ወይም ጠበቃውን እንደገና ማነጋገር ከፈለጉ፣ ፖሊስ እንደገና እንዲያነጋግረው ወይም እንዲያነጋግራት መጠየቅ ይችላሉ። ፖሊስ አንድ ጊዜ ካነጋገራቸው በኋላ ጠበቃው ፖሊስ ጣቢያ ሲደርስ አስተያየት የመስጠት መብት የለውም። ከፈለጉ ፖሊስ የእርስዎን ሃሳቦች እና ምኞቶች ለዚህ ጠበቃ ማጋራት ይችላል።

**ቅሬታ የማቅረብ መብትዎ**

- በፖሊስ ስለተስተናገዱበት መንገድ ቅሬታ የማቅረብ መብት አለዎት።
- ስለ ስኮትላንድ ፖሊስ ቅሬታ ካቀረቡ ይህ በመጥፎ እንዲታዩ አያደርግዎትም።
- በጥበቃ ስር ሆነው ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ።
- በጥበቃ ስር እያሉ ቅሬታ ማቅረብ ከፈለጉ፣ ከመርማሪው ወይም ከፍተኛ ደረጃ ካለው ሰው ጋር ለመነጋገር ይጠይቁ።
- ከተለቀቁ በኋላ ቅሬታ ማቅረብ ከፈለጉ፣ ወደ ማንኛውም ፖሊስ ጣቢያ መሄድ ይችላሉ።
- በተያዙበት ወይም በፖሊስ ቁጥጥር ስር በነበሩበት ጊዜ በአንድ የፖሊስ መኮንን የመቁሰል ወይም ጉዳት ከደረሰብዎ ለስኮትላንድ ፖሊስ የሙያ መስፈርቶች መምሪያ ቅሬታ ማቅረብ አለብዎት።
- ቅሬታ ለማቅረብ ወደ 101 ይደውሉ ወይም ወደ አካባቢዎ ፖሊስ ጣቢያ ይሂዱ።
- በተጨማሪ ሌላ ሰው ቅሬታ እንዲያቀርብልዎ መጠየቅ ይችላሉ። ወላጅ፣ ጓደኛ፣ አጋር ወይም የሚያምኑት ሰው ሊሆን ይችላል። የእርስዎን በጽሁፍ የቀረበ ፈቃድ ሊሰጧቸው ይገባል።

ይህ በራሪ ወረቀት ከህጻናት እና ወጣቶች የፍትህ ማዕከል (CYCJ) እና ከስኮትላንድ መንግስት ጋር በመተባበር፣ የአስተማማኝ እንክብካቤ ተሞክሮ ላላቸው ሰዎች በስኮትላንድ ብቸኛ አዘጋጅ ቡድን በሆነው፣ በ STARR አባላት በጋራ ተዘጋጅቷል። 'ቅሬታ የማቅረብ መብትዎ' ከPeople First Scotland ጋር የሚስማማ ነው።

ለተጨማሪ መረጃ እና ድጋፍ **justtherightspace.org** ን ይጎብኙ።

© Crown copyright 2023

Children and Young People's Centre for Justice

Safer Scotland
Scottish Government